የማለዳ ወግ...

# የህዝብ እውነት፣ አጋርነትና የወደድኩት የሙሽሪት ትጋት!

= = = = = = = = = = = = = = = = = = = = = = = = = = = = =

* የህዝቡ ስሜት በየፈርጁ ይገለጻል፣ ዛሬም ጀግና ሙሽራ አየን!
* ከሪዮ እሰከ ዲሲ፣ ከአማራ እሰከ እስከ ኦሮሚያ የህዝብ ሀቅ!
* እጁን ቆልፎ "አቅመ ቢሶች ነን፣ ታስረናል!" ሲል "አሸባሪ ነህ" አትበሉት
* ስማን " ሰከን በል" ዘማች ፣ አዝማች ወታደሩ ፣ ሰከን!!!

በደል፣ ጭቆናና አድልኦና ግፍ በከፋ ቁጥር ሀገሬው የጭቆና ቀንበር መሸከሙን አሻፈረኝ ይላል ... የሰላም በሮች ሲዘጉ፣ ለእንቢተኝነት በሮችን ይከፍታሉ! ሀገሬው እየተቀጠቀጠ እየተገዛም እንቢተኝነቱን በተለያዬ ፈርጁ ብዙ መንገዶች ጉዳት ስሜቱን ሳይፈራ ደፍሮ ይገልጻል። ብዙዎቻችን ህመሙ እያመመን ሳንገልጸው፣ አለያም ሆድ አደር ሆነን ስንንከላዎስ የወገናቸውን ትክክለኛ ብሶት ፣ የህዝብ እውነት ፣ የአጋርነት ድምጽ በተለያዩ አጋጣሚዎች የገለጹ በእርግጥም የታደሉ ናቸው! በቅርብ ወራትበፊት በሪዮ አትሌት ፈይሳ ሌሊሳ ባሳለፍነው ሳምንት ደግሞ በዲሲ በአንዷት መልከ መልካም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊት ሠርግ ላይ ያየነው ነፍሳችን በሃሴት ነጥቆናል ፣ እናም ከሪዮ እስከ እሰከ ዲሲ፣ ከአማራ እሰከ እስከ ኦሮሚያ የተመለከትነው የህዝብ አጋርነት የህዝብ እውነት እውነታችን ነውና የሀገረ አሜሪካ የዲሲዋን ሙሽራ በዛሬው የማለዳ ወግ ክብር ሰጥተን እናወሳታለን!



"ሰከን በል" የሚለውን የአርቲስት ይሁኔ በላይን ወኔ ቀስቃሽ ወቅታዊ ዘፈን በሠርጓ ቀን እንዲዘፈን የመረጠችው ሀገር ወዳድ አስገራሚና አስደናቂ ሙሽራ ቪዲዮ የደረሰኝ ከትንናት በስቲያ ነው፣ መረጃውን ያደረሱኝ ደግሞ እዚህ ሳውዲ የሚገኙ ቤተሰቦቿ ናቸው። ስመለከተው በስሜት የሸነቆጠኝን የሙሽሪት ልዩ የሀገር ፍቅር መግለጫ የሆነውን የሙሽሪት የሠርግ ቀኗ ምርጫ" ሰከን በል " ጣዕመ ዜማ ልዩ መልዕክት የሰማሁት በመሪሩ ሀዘን ሳምንት መካከል ቢሆንም ዜማው ከፈንጠዝያና ዳንኪራ የወጣ መልዕክት አለውና ከሙሽሪት ወኔ ጋር " ሰከን በል" ሰከን በል እያልን ስለሚያገባን እናዎጋለን ...!

የሙሽሪት ሜሮንን ቪዲዮ እንዳሰራጨው ጠየቄ በሙሽሪት ቤተሰቦች በኩል ሙሉ ፈቃድ ሰጥተውኝም ነበር ። ቢሸፍቱ አልቅሳ ቀኑ ጥቁር የሀዘን ቀን ስለነበር ከማሰራጨት ወኔውን አጣሁት... መረጃው ሲደርሰኝ ሠርጉ በሃገረ አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ እንደተከወነ የገለጸችልኝ እህቷን የሙሽሪትን ሙሉ ስሟን ማን ይባላል ስል ጠየቅኋት፣ መለሰችልኝ "በስሟ ትገረማለህ ሜሮን መሀመድ ያሲን ትባላለች፣ ለእኔ የእናቴ ልጅ ናት በአባቷ አፋር ናት፣ እሷ ግን ክርስቲያን ናት፣ መቼም ኢትዮጵያ ውስጥ የቀራት ገድማት ቤተክርስቲያን የለም፣ እንደሚመስለኝ ብቸኛዋ የአፋር ክርስቲያን እሷ ናት!" አለችኝ! ተደመምኩ፣ አፋሮች ሲነሱ አባት አሊ ሚራህ ትዝ ይሉኛል፣ "የኢትዮጵያን ባንዴራ እንኳን እኛ ግመሎቻችን ያውቋታል!" ሲሉም በቦታው ነበርኩ! አሳይታ ... የአፋሯ ሙሽራ ስለ ኢትዮጵያ የሆነችውን ብትሆን እሷ የጀግኖች ዘር መሆኗ ነው አክኩና አሁንም በሰማሁት ታሪክ ተደመምኩ!

ብቸኛዋ የአፋር ክርስትያን ልትሆን የምትችለው ሙሽሪት ሜሮን ዛሬ የወገኗ ነገር አንገብግቧት "ሰከን በል" እያለች በሠርጓ አዳራሽ በስሜት ስትውረገረግ፣ እጆችዋን ወደ ላይ ከፍ

አድርጋ ከነሚዜዎቿ በማንሳትና በማቆላለፍ ከህዝቡ ጋር መሆኗን በልዩው የሠርጓ ቀን በወኔ ተሞልታ ስታሳይ አለቀስኩ ... በሚታየው ጥልቅ ስሜቷ ውስጤን ነካችውና ሆዴ እንደ መባባት አለ ...

"ሰከን በል" የሀገር ወዳዱ የታዋቂው ዘፋኝ የይሁኔ በላይ የአዲስ አመት ልዩ ማስታወሻ ቢሆንም ሰከን ባላለው ወታደር ህዝብ እየተጨፈጨፈ ላዘነ ለተቆጨና እንደኔ ቆሽቱ ላረረው ጥሩ ስሜት መግለጫ ሆኖም ሰንብቷል ... ዛሬ በሙሽሪት እጅ በአዳራሹ ገብቷል ... ሙሽሪትን ደጋግማ " ሰከን በል " ስትል ስማኋት፣ ከአርቲስት ይሁኔ ድምጽ እኩል ስታዜመው "ሰከን በል" ስትል ሰማኋት ፣ ሰከን ማለት ደግሞ ግድ ይላል ! ወታደሩ ሰከን በል ፣ ገዳይ አስገዳይ ጨምላቃው ፖለቲከኛም ሰከን በል፣ የሚሞተው ወንድምህ ነው ፣ የሚሞተው እህት ናት ፣ እናም ሰከን ማለት ይበጅሃል ፣ ሰከን በል ! ስትል እስክታውን በቁጭት ስታስነካው የፈንጠዝያና ዳንኪራ ስሜት ላለመሆኑ ያሳብቅባታል!

የሰከነ ነገር ጠፍቶ ...እዚህም እዚያም ግፍ በዝቶ የማንፈልገውን እንድንደግፍ ፣ እንድንመርጥ እየተገፋን ነው ...የምንወዳት ሀገራችን ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ መኳዝን በውል ለታዘበ ይህ እውነት የማያንገበግበው ወገኔ የለም ፣ እናም ሙሽሩት ሜሮን አንዷ ናት ፣ የሙሽሪት ሜሮን ሰከን በል ምርጫ ከእነ ሙሉ እንቅስቃሴዋ እየተመለከትኩ በሙሉ ሀገራዊ ወኔ በሀዘን ውስጥ ሆኖም በቁጭት እልህ ጥልቅ ስሜት ተዘፍቆምና በሀዘን ስሜት ውስጥ ገብቶ በእልህ ይነሽጣል ...

ይሁኔና ሙሽሪት "ሰከን በል" እያሉ ባንድ መድረክ የተጫወቱትን ያህል ሰርጾ ሊገባ የቻለው እንቅስቃሴ መሰረቱ በውስጡ ያለው እውነት ለመሆኑ አልጠራጠርም ። በሙሽሪት የደስታ ቀን በሀገር ስሜት ዋጅታ በነፍሷ አልፎ በፊቷና በመላ አካሏ የሚታየው ቁጭት ብሎም የወገናዊነት ፣ የህዝባዊነት ስሜት እውነት ቁልጭ ብሎ በሙሽሩት ላይም ይታያል ! ያ ብዙዎች ዘንድ በጥቂቶች ላይ ያደረው የወገናዊነት " ያገባኛል "ስሜት እውነት በእርግጥም በሙሽሪት ይገለጻል! በሀገረ አሜሪካ በዲሲ ከተማ በታላቁ የሙሽሪት የደስታ ቀን የሠርጓ እለት አብሮበትና ከህዘብ አጋር መሆን ስለእውነት እንዲህ ወኔን ቀስቃሽ ሆኖ ጀግንነት በየፈርጁ እንድናይ ምክንያት የሆነችውን ሜሮን ጀግና የእኛ ሙሽራ ብያታለሁ :)

ሙሽሪት ሜሮን "በሰከን በል" ልዩ ሀገራዊ ጣዕመ ዜማ ያንጸባረ ቀችው ሀገሬ ተጎዳች በሚል ቁጭትን " መለያየት አይጠቅምም በማለት ነበር ...

"ድር እንኳን ቀጭኑ ድር እንኳን ለስላሳው
ሲያምር ሲተባበር ይበልጣል ካንበሳው" ይል ዘንድ ይሁኔ በሜሮን ሰርግ አብሮነትና የሀገር ፍቅርን በልዩ መሳጭ ስሜት ተሰብኳል!
"ወታደሩ ሰከን በል
አፈሙዙን ሰከን ዐርገዉ
ቃታዉን እንዳትስበዉ
ቢዶ እጅን ነው እሚጮኽው
ሠላማዊ ወንድምህ ነዉ" ተብሎም ወታደሩ "ተረጋጋ፣ ሰከን በል" ትበሎ ወታደሩ ምክር ሲለገሰው "ሰከን ማለት ነው ጀግንነት" ተብሎ በሰርጉ አዳራሽ በህበረት ተስተጋብቷል ፣ ያውም በልዩው የግሏ የደስታ ቀን ...! ጀግናዋ የኢትዮጵያ ሙሽራ!

ህዝቤን ተውት እንዲል ደጉ አባት ... ባለቅኔው አንጎራጓሪ "ሰከን በል" ሲል በሰራው ነጠላ

ዜማ አዛዥ፣ ገዳይ፣ አስገዳይ አዛዦችም እንዲህም ተብለዋል በይሁኔ ማራኪ ጣዕመ ዜማ
"ሰከን በሉ ህዝቤን ተዉት
ድምጹን ስሙት፣ አትግደሉት
መንግስት በአገሩ በህዝብ ላይ አይተኩስ
ዘር አጥያት ይሁን ንጉስ ከማሪዮስ" የተባለው በሙሽሪት ሠርግ ላይ ደምቆ ሲሰማ ማስተዋል፣ በተበደለ ህዝቧ የተጎዳ የሙሽሪትን ስሜት ማየት ያልቻላችሁ ካላችሁ ስሜታችሁን ፈልጉት … እኔ ይህን የሙሽሪትን ሠርግ "ሰከን በል!" ምርጫና፣ የመልከ መልካሟን እህት ውስጥና ውጫዊ ስሜት ተረድቸው ረክቸበታለሁ!

ሰሚ ቢገኝ ሀገሬው በደስታ በሀዘን፣ በየተናጠል በህብረት ስሜት ፍላጎቱን ፣ የዲሞክራሲ ጥማት ነጻነቱን እየጠየቀ ነው፣ ሆዳም ካልሆነው ተትረፍርፎ ከሞላው እስካጣ የነጣው እጁን ወደ ላይ በማንሳት "አቅመ ቢሶች ነን፣ ታስረናል!" ብሎ የተቃውሞ ድምጹን ሲያሰማ "አሸባሪ ነህ" አትበሉት! የውስጥ እውነቱ፣ የተቃውሞ ህብረቱ መገለጫ ምልክት አድርጎታልና እየመረራችሁም ቢሆን ተቀበሉት!

ሙሉ የሙሽሪት ሜሮንን ቪዲዮ እንዳሰራጨው ጠየቄ በሙሽሪት ቤተሰቦች በኩል ሙሉ ፈቃድ ሰጥተውኝም ነበር ። ቢሸፍቱ አልቅሳ ቀኑ ጥቁር የሀዘን ቀን ስለነበር ከማሰራጨት ወኔውን አጣሁት … መረጃው ሲደርሰኝ ሠርጉ በሃገረ አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ እንደተከወነ የገለጸችልኝ እህት የሙሽሪትን ስሟን ማን ይባላል ስል ጠየቅኳት ፣ መለሰችልኝ " በስሟ ትገረማለህ ሜሮን መሀመድ ያሲን ትባላለች፣ ለእኔ የእናቴ ልጅ ናት በአባቷ አፋር ናት፣ እሷ ግን ክርስቲያን ናት፣ መቼም ኢትዮጵያ ውስጥ የቀራት ገድማት ቤተክርስቲያን የለም፣ እንደሚመስለኝ ብቸኛዋ የአፋር ክርስቲያን እሷ ናት!" አለችኝ! ተደመምኩ፣ አፋሮች ሲነሱ አባት አሊ ሚራህ ትዝ ይሉኛል፣ "የኢትዮጵያን ባንዴራ እንኳን እኛ ግመሎቻችን ያውቋታል !" ሲሉም በቦታው ነበርኩ ! አሳይታ …

ብቸኛዋ የአፋር ክርስትያን ልትሆን የምትችለው ሙሽሪት ሜሮን ዛሬ የወገኗ ነገር አንገብግቧት "ሰከን በል" እያለች እጆችዋን ወደ ላይ በማቆላለፍ ከህዝቡ ጋር መሆኗን በልዩው የሠርጓ ቀን በወኔ ተሞልታ አሳይታናለች ፣ እናመሰግናለን !

እናንተም! ሙሽሪትን ስሟት!" ሰከን በል" ትላለች፣ ሰከን ማለት ደግሞ ግድ ይላል! ወታደሩ ሰከን በል፣ ገዳይ አስገዳይ ጨምላቃው ፖለቲከኛም ሰከን በል፣ የሚሞተው ወንድምህ ነው ፣ የምትሞተው እህትህ ናት፣ እናም ሰከን ማለት ይበጅሃል፣ ሰከን በል!

ለጀግናዋ ሙሽራ መልካም ጋብቻ ተመኘሁ!

ሰናይ ቀን!

ነቢዩ ሲራክ
መስከረም 24 ቀን 2009 ዓም